ሳምንታዊ ዜና (ሚያዝያ 11 ቀን 2000 ዓ. ም.)

በአዲስ አበባ የቦምብ ፍንዳታዎች ደርሰው የአስር ሰዎችን ህይወት ቀጠፉ፣ በርካቶች ለጉዳት ተዳረጉ፣ አደጋውን ያደረሰው የወያኔ ቡድን መሆኑ ተነገረ፣ አፈሳው ተጡዋጡፎ ቀጥሎዋል፣ የአዲስ አበባ እስር ቤቶች ተጣብበዋል፣ በኦጋዴንና በሁመራ ውጊያ መኖሩ ተጋለጠ፣ የሶማሌ ክልል ምክር ቤት ስድስት አባላት ያለመከሰስ መብታቸው ተገፍፎ ተባረሩ፣ የግብጹ ጳጳስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ የተያዘላቸው የጉብኝት ፕሮግራም በጸጥታ ችግር ሳቢያ ተሰረዘ »»»»»»»»»»»»»»

ሌላም ዜና ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ያንብቡ ……………………..……....

ሚያዝያ 5 ቀን 2000 ዓ.ም ወያኔ ብቻውን ሮጦ ብቻውን ያሸነፈበት የምርጫ ሂደት ካበቃ ከምሽቱ 12 ሰዓት ተኩል በኋላ በአዲስ አበባ ሲቪል የለበሱ የፖሊስ አባላትና ደህንነቶች በጥምረት በተለያዩ አካበቢዎች እየተዘዋወሩ የመረጠውንና ያልመረጠውን ቀለም ስለመቀባቱ የአውራ ጣቱን እያዩ ከመንገድ ላይ እያፈሱ ወዳልታወቀ ስፈራ እየወሰዷቸው እንደነበር ታወቀ::

«የሚወክለኝ ስለሌለ መምረጥ አልፈልግም» በማለት ከ95 በመቶ በላይ የሆነው የሃገሪቷ ሕዝብ ወደ ምርጫ ጣቢያ ያልሄደ ሲሆን፣ በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ መራጭ የሌለ ከመሆኑም በላይ የራሳቸው የወያኔ ደጋፊና አባሎች ብቻ ምርጫውን ያካሄዱ ሲሆን ከ12 ሰዓት በኋላ በወያኔ ካድሬዎች ትዕዛዝ ሕዝቡ ባለመምረጡ ተናድደው ከየመንገዱ እያፈሱ እንዲታሰርና እንዲደበደብ ማድረጋቸውም የችግሩ ሰለባ የሆኑ ወጣቶች አጋልጠዋል::

ከመገናኛ እና አያሬ ሰፈር የተያዙት ሰላማዊ ሰዎች ወደ ፈረሰኛ ወይም አብነት አካባቢ ጀስ ሃንሰን ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በተቁዋቁዋመው አዲስ የፌዴራል ፖሊስ ማዘዣ ጣቢያ ካምፕ ውስጥ አስገብተው «ለምን በምርጫ ላይ አልተሳተፍክም» በሚል ሌላ ተጨማሪ ጥያቄ ሳያቀርቡ ባልተወለደ አንጀታቸው ከፍተኛ ድብደባ ያካሄዱበት ሲሆን፣ ድብደባ የሚያደርጉት ደግሞ በጥቁር የጐማ ዱላ እንደሆነና ይህ ጐማ ውጫዊውን የሰውነት አካል እንዳያደማ ነገር ግን ውስጣዊ ጉዳት እንዲያደርስ ሆን ተብሎ የተዘጋጀ በመሆኑ ወጣቶች በዚህ ድብደባ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው ለቤተሰቦቻቸው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል::

በዚህ አይነት በተለያዩ ካምፖች ታፍሰው እንዲህ አይነት ተመሳሳይ እርምጃ የተወሰደባቸው በሺህዎች የሚቆጠሩ መኖራቸውን ለማወቅ ተችሎዋል::

በማግስቱ ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን 2000 ዓ.ም ከጧቱ 12 ሰዓት ጀምሮ ወያኔዎች በጠብመንጃ እየተጠበቁ በሰቀቀን በሚኖሩበት ቤተ መንግስት ዙሪያ ጥበቃ ላይ የተሰማሩ ቀይ ቆብ የደፉ ወታደሮችን ጨምሮ የፌዴራል ፖሊሶች ከወትሮው በተለየ መልኩ አዲስ አበባን ወጥረው ይዘዋት እንደዋሉም የአይን ምስክሮች ገልፀዋል፡፡

በአዲስ አበባ በሁሉም አካባቢዎች በወታደራዊ ፓትሮል እና ከ5 ሜትር እስከ አስር ሜትር ርቀት ውስጥ አንድ ሙሉ ትጥቅ የታጠቀ እግረኛ ወታደር ጥብቅ ጥበቃ እንዲደረግ በታዘዘው መሰረት ተግባራዊ ሲያደርጉ የዋሉ ሲሆን ጥበቃቸው ወትሮ ከነበረው እጅግ የተለየ እንደነበረም የአይን እማኞች አጋልጠዋል፡፡

ይህ ሆኖ በዋለበት በዚህ እለት ከምሽቱ 12:30 እስከ ምሽቱ 1 ሰዓት ድረስ በ3 የተለያዩ ቦታዎች ፍንዳታ መድረሱና በርካታ ሰዎች ለሞትና ለከፍተኛ ጉዳት መደረጋቸው ታውቋል፡፡

በለም ሆቴል አካባቢ በሚገኘው ኖክ የነዳጅ ማደያ፣ ወደ ገርጂ ኢምፔሪያል ሆቴል አቅራቢያ በሚገኘው የኖክ ነዳጅ ማደያ እንዲሁም በሲ ኤም ሲ አካባቢ ፍንደታዎቹ የደረሱ ሲሆን በሶስቱም ቦታዎች የንፁሃን ዜጐች ጉዳት እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዕለቱ ከ10 ሰዎች በላይ ንጹሃን ሰዎች እንደሞቱና ከ25 ሰዎች በላይ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸው የተለያዩ ሆስፒታል ውስጥ የገቡ ሲሆን፣ በተለይም ምኒልክ ሆስፒታል የገቡት ቁስለኞች ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸውና ከእነዚህም መካከል አንደኛው ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን ህይወቱ ማለፉ ታውቋል፡፡

ወያኔ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ባደረኩበት ማግስት ይህን የመሰለ ጥቃት በአሸባሪዎች ተሰነዘረብኝ እያለ ያላዝን እንጂ በእለቱ ከነበረው የጠነከረ ጥበቃ አንጻር ፍንዳታው ምሽት ላይ ከመድረሱ አስቀድሞ የሆነ በመሆኑ ፍንዳታውን ራሱ ወያኔ ያደረሰው ስለመሆኑ የሚያመላክት ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ኗሪዎች በተፈጸመው ድርጊት አዝነው ሲናገሩ ተደምጠዋል

ለዚህም ይመስላል መላው የሃገሪቷ ሕዝብ በወያኔ ቴሌቭዥን የተደሰኮረውን አላምንም ያለውና አባባሉም ያልተዋጠለት

ወያኔ በደረሰበት ከፍተኛ የፖለቲካ ኪሣራ እና በተለይ በሰራዊቱ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ የመጣው የእርስ በእርስ ሽኩቻን ለማረጋጋት ሲል ብቻ ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ እንዳደረገው ሁሉ ዛሬም ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት አልሞ በንፁሃን ኢትዮጵያውያን ላይ ይህን የመሰለ ዘግናኝ እልቂት እንዲደርስ ማድረጉ በእጅጉ የሚያሳዝን ከመሆኑም በላይ ልብ የሚያደማ ታሪክ ይቅር የማይለው መሆኑን ዘጋቢያችን ተዘዋውሮ ያነጋገራቸው የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በእልህና በቁጭት ገልጸውለታል::

የሚገርመው እራሱ ድርጊቱን ፈፅሞ መልሶ ጩኸቱን ቀሙኝ እንዲሉ ምሽቱን ድርጊቱ መፈፀሙን ከገለፀ በኋላ በዚያው ቅጽበት በመላ አዲስ አበባ ጥብቅ ፍተሻ ተደርጎ በርካታ ንፁሃን ዜጐች ከመንገድ ላይ እየታፈሱ ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውን የአይን እማኞች ገልፀው ጥቂት የማይባሉ ባለ መኪናዎችም ከእነ ንብረታቸው ከሁለት አጃቢ ጋር እነሱ ወደ ሚመሩህ ሂድ እየተባሉ ከመንገድ ላይ ታፍሰው መወሰዳቸው ታውቋል::

መለስና ቡድኑ ከበረሃ ጀምረው በውሸት ላይ በተመሰረተ ፖለቲካቸው እስከ አሁን ድረስ የመጡ ቢሆንም ዛሬ ውሸታቸው ተጋልጦ ሁሉም ገሀድ ሲወጣ በሠራዊቱ ውስጥም ጥያቄውና የእርስ በእርስ ሽኩቻው ሲጀምር እነሱን ለማረጋጋትና የፖለቲካ ጠንቆች ናቸው አይበጁኝም የሚላቸውን ኢትዮጵያውያን ለማደን እንዲያመቸው ይህንን ዘግናኝ እርምጃ መውሰዱ አረመኔነቱን በጉልህ ያሳየበት ነው የሚሉ ታዛቢዎች በርካቶች ናቸው::

ይህ ክስተት ሰኞ ሚያዝያ 6 ቀን ምሽት ላይ የተካሄደ ሲሆን በድጋሚ በማግስቱ ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም በላፍቶ አካባቢ እንዲሁ ተመሳሳይ የሆነ ፍንዳታ መከሰቱ ታውቋል:: በዚህ በደረሰው ፍንዳታ በርካታ ሰዎች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑንም የደረሰን ዘገባ ገልፆ በወቅቱ የሞተ እንዳልነበረም ተገልጿል::

ወያኔ በሕዝቡ ተጠልቶ መድረሻ ያጣ የሕዝብ ድጋፍ የሌለው መናጢ ሲሆን፣በተለይም አሁን ብቻውን ተወዳድሮ ብቻውን ባሸነፈበት ምርጫ እንኩዋን የገዛ ጥላውን አላምን እያለ እየደነበረ ያገኘውን የግፍ እርምጃ ሁሉ እየወሰደ ሲሆን፣ የአሁኑ ዘግናኝ እርምጃ ግን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አሰቃቂና ሰቅጣጭ መሆኑ ያሳዝናል ሲሉ የህብረተሰቡ ክፍሎች በአዘኔታ እየገለፁ ናቸው::

እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት ከሆነ ወያኔ ማንም ከልካይ የሌለው ያሻውን እርምጃ የሚወስደው ደንቆሮና ልበ ድፍን ቡድን ሆኖ ሳለ ሰበብና ምክንያት ይሆነኛል በማለት ይህን የመሰለ ምንም በማያውቁ ዜጐች ላይ ጨካኝ እርምጃ መውሰዱ ቡድኑ ደም የጠማው የሰው አውሬነቱን ያረጋገጠበት ነው ብለዋል።

በአሁን ሰዓት ከእሁድ ሚያዝያ 5 ቀን ምሽት ጀምሮ እስከ ረቡዕ ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ብቻ ታፍሰው የተወሰዱ ዜጐች ቁጥራቸው በሺህ የሚቆጠሩ ሲሆን፣ ማዕከላዊ ምርመራን ሳይጨምር አዲስ በተሰሩት 43 እስር ቤቶችና ሌሎችም የቆዩ እስር ቤቶች ውስጥ ታጉረው እንደሚገኙም የፖሊስ ምንጮች ከመግለጣቸውም በላይ እስር ቤቶቹ ከመሙላታቸው የተነሳ ቁጭ ለማለት እንኳዋን እንደማይቻል አስረድተዋል። ከራሱ ጥላ ጋር ብቻ ተወዳድሮም እንዲህ ዜጎችን ለመጨፍጨፍ የበቃው ወያኔ የዘንድሮውን የሰላማዊ ዜጎች ደም መጠጣት በጀቱን በዚሁ ቢበቃው እንዴት ጥሩ ነበር ዳሩ አይጠረቃም እንጂ ሲሉ የተናገሩም አልጠፉም

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሌሎችም አጨብጫቢ ካድሬዎች ሃገሪቷ ሠላም ነች በልማት ጉዳና ላይ ነች እያሉ የአለምን ሕብረተሰብ ሃሳብ ለማስቀየር ቢወተውቱም እንደ ረመጥ እሳት 360 ዲግሪ ወያኔ ተወጥሮ የሚያደርገው ሲያጣ ንፁሃን ዜጐችን እየጨረሰ ሕዝቡን እያሰቃየ መገኘቱ የወያኔ መሪዎች የእብደታቸው ምልክት ነው የሚሉት በርካታ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ናቸው።

ምርጫ ተብየውን ሚያዝያ 5 ቀን ከማድረጉ ሁለት ቀን ቀደም ብሎ ሚያዝያ 3 ቀን የወያኔ ዕጩዎች የሻማ ማብራት ፕሮግራም አድርገው ሕዝቡን ለመቀስቀስ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በራፍና በምስካየ ኅዙናን መድሃኒያለም ትምህርት ቤት በር አካባቢ ባደረጉት ሙከራ ተማሪዎችም ሆነ ቤተክርስቲያን ለመሳለም የነበረው ሕዝብ በቁጣ ወጥቶ በድንጋይ ያባረራቸው ሲሆን ጥቂት የማይባሉ የወያኔ ቡችሎችም ጉዳት እንደደረሰባቸው ያስታወሱት አንድ የተፈሪ መኮንን መምህር ወያኔዎች የሚያደርጋቸውን

አሳጥቷቸዋል ከዚህ በኂላ እራሳቸውን በራሳቸው አፈንድተው እስኪጨርሱ ትዕግስት አድርገን መጠበቅ ነው:: ይህ ደግሞ አይቀሬ ነው ሲሉም ገልፀዋል::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሰሞኑን ከኒውስዊክ ከተሰኘው መፅሄት ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ በሃገሪቷ ሠላም የሰፈነ መሆኑን፣ በኦጋዴንም የተቃዋሚውን ድርጅት አከርካሪው እንደተመታ እና የዲሞክራሲ ግንባታው ተጠናክሮ እንደቀጠለ የሃሰተኛ ፕሮፓጋንዳውን ቢለፍምም ያለው እውነታ ግን ከዚህ የተለየ መሆኑን አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር አጋለጡ::

የሃገሪቷ ሕዝብ የሚቀምሰው ሊያጣ እየተቃረበ ባለበት በዚህ ወቅት ይባስ ብሎ የወያኔው ቡድን በሕዝቡ ላይ በፈጠረው ጫና ምክንያት እንደልቡ መግባትና መውጣት ተከልክሎ ያለበት ደረጃ ላይ መደረሱን ገልፀው የዕለት ጉርሱን እንኳዋን እንዳያሰላስል ጫና የተደረገበት መሆኑን ገልፀዋል::

በተለይም በምስራቅ ኢትዮጵያ በኩል የሚገኘውን የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር እንቅስቃሴ አፅድቻለሁ በማለት ለታወቀው መፅሄት መለስ ዜናዊ መግለጫ መስጠቱ በጣም አሳፋሪና እና ውሸት ከመሆኑም በላይ አንድ የሃገር መሪ ነኝ ከሚል ግለሰብ የማይጠበቅ ነው ካሉ በኂላ ሌላው ቢቀር ከመፅሄቱ ጋር ቃለ ምልልስ ባደረገበት ወቅት እንኳዋን ውጊያ ላይ እንዳለ በቂ መረጃ አለኝ ሲሉ አብራርተዋል:: ውሸት የለመደ ሌላምን ሊል ይችላል ሲሉም እኒሁ ምሁር አክለው ትዝብታቸውን አጋርተዋል

ሌላው መለስ ሠላም አስፍነናል ባለበት ወቅት የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ፀጋዬ በርሄ የተባለው የወያኔ ባለሥልጣን በትግራይ መቀሌ ተካሂዶ በነበረው 3ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ « የትግራይ ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ነቅቶ መጠበቅ ያለበት የኦጋዴንን ፅንፈኛ ቡድን ነው» በማለት የአለቃውን አባባል ሙሉ በሙሉ አጣጥሎታል::

በተያያዘ ዜና በአሁን ሰዓትም በኦጋዴን ከፍተኛ ውጊያ እየተካሄደ መሆኑንና በርካታ የጦር መሣሪያና ወታደሮች ወደ ኦጋዴን እየተጓጓዘ መሆኑን የመከላከያ ምንጮች ገለፁ::

በሠራዊቱ ውስጥ በተፈጠረው የሞራል ልሽቀት የተነሳ ጦሩ እንደቀድሞው የውጊያ ብቃት የሌለው ከመሆኑም በላይ እርስ በእርሱ በአይነ ቁራኛ እየተያየ እራሱን ጠላት ከሚለው ወገን እንኩዋን መጠበቅ ተስኖት በተለይ ከሚያዝያ 1 ቀን እስከ ሚያዝያ 3 ቀን 2000 ዓ.ም በተደረገው ውጊያ በርካታ ወታደሮች ቆስለው ወደ ሐረር መምጣታቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ይህ ውጊያ ተጠናክሮ በቀጠለበት በአሁን ሰዓት የሱማሌ ክልል ምክር ቤት ተብየው 6 የምክር ቤቱ አባላት ከኦጋዴን ነፃነት ግንባር ጋር ግንኙነት አላችሁ በማለት ያለመከሰስ መብታቸውን አንስቶ በቅርቡ ተከስሰው ወደ ዘብጥያ ሊያወርዳቸው እንደተዘጋጀ ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገልጿል፡፡

እንደደረሰን ዘገባ ከሆነ ከዚህ ቀደም መኮንኖችን ጨምሮ 150 የፖሊስ አባሎችን በእንዲህ አይነት ሁኔታ ለእስር የደረጋቸው ሲሆን፣ አሁን ደግሞ የራሴ ናቸው ብሎ ምክር ቤት ያስቀመጣቸውን 6 ሰዎች ያለመከሰስ መብታቸውን ካነሳ በኋላ ሰሞኑን ከስሶ ለፍርድ አቀርባለሁ እያለ ባለበት ወቅትም የጅጅጋ ታዋቂ ነጋዴዎችም በደህንነት በየቀኑ ክትትል እየተደረገባቸው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

እነዚህ የደህንነት አባሎች የትግራይ ተወላጆች የሆኑ እና የወያኔ ስርዓት ቤተ መንግስት እግሩ ሲገባ ጀምሮ በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩና የሱማልኛ ቋንቋ መስማትና መናገር የሚችሉ መሆኑን የደረሰን ዘገባ አስረድቶ በአሁን ወቅት ከ50 የማያንሱ ለዚሁ ተግባር የተሰማሩ የወያኔ ደህንነቶች በጅጅጋ ከተማ እንዳሉ አብራርቷል፡፡

ሌላው ደግሞ ሰሞኑን የአልጄዚራ ቴሌቭዥን ሪፖርተሩን በረሃ ድረስ ልኮ የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጭ ግንባር ተዋጊዎች ናቸው የተባሉትን ያነጋገረ ሲሆን በአሁን ሰዓት ከቀላል መሣሪያ እስከ ከባድ መሣሪያ የታጠቁ መሆኑንና ቁጥራቸው ለጊዜው ያልታወቀ የተዋጊ ኃይል መኖሩን በይፋ አጋልጧል፡፡

ይህ እየሆነ ባለበት ወቅት በሁመራ የታጣቂ ቡድን አባሎች መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሠላም ማህበር የተባለው የወያኔ ንብረት የሆነ አውቶብስ ላይ ፍንዳታ ያደረሱ ናቸው በማለት 6 ወጣቶችን በቴሌቭዥን ያቀረባቸው ሲሆን፣6ቱም ወጣቶች ከትግርኛ በስተቀር አማርኛ እንደማያውቁ ተገልጿል፡፡

ወያኔ እራሱ እያፈነዳ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ አገኛለሁ በሚል ምንም የማያውቁትን እየደለለ መልሶም እያፈሰ የቁም ስቃያቸውን እያሳያቸው ሲሆን

አሁንም የተሰራው ድራማ ከዚህ የተለየ አይደለም ሲሉ ሁኔታውን የተከታተሉ ወገኖች ገልፀዋል።

በአንጻሩ የሰላምን አውቶብስ ሲያፈነዱ ያዝኩዋቸው ተብሎ ምስላቸው የታየው የትግርኛ ቋዋንቋዋ ተናጋሪዎች በመሆናቸው ለድራማው ማሳመሪያ ንጹሃንን አስገድዶ ተጠቅሞባቸዋል ለማለት አያስደፍረኝም ያሉ አንድ ስማቸው እንዲገለጽ ያልፈቀዱ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፖለቲካ ሳይንስ ምሁር ምስላቸው የታየው በሙሉ ማለትም ስድስቱም የወያኔ የጥፋት ተላላኪዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ በግሌ እገምታለሁ በማለት መናገራቸውን ከዘገባው ለመረዳት ተችሎዋል

በተመሳሳይ ሁመራ እና ወልቃይት ጠገዴ ውስጥ በየቀኑ የተኩስ ልውውጥ እየተደረገ ሲሆን፣ በየቀኑም የወያኔ ወታደር እየሞተና እየቆሰለ ወደ ኋላ ወረዳ እየተወሰደ መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

ሕዝቡ የሚቀምሰው አጥቶ ተቸግሮ ባለበት በዚህ ወቅት ከጉንደር ክፍለ ሃገር ላይ ገንጥሎ የወሰደው የወልቃይት ጠገዴን ሕዝብ አስገድዶ ገንዘብ እንዲያዋጣ መደረጉ ተጋለጠ።

በዚህም መሠረት ሁሉም የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪ በሙሉ እናትም መቀነቷን ፈትታ፤ አባት ኪሱን ገልብጦ በግዳጅ እንዲከፍሉ በተደረገው መሰረት ካድሬዎቹ አልበቃንም ጨምሩ ማለታቸውን ቀጥለዋል እንጂ እስከ አሁን ድረስ 744 ሺህ ብር ከሕዝቡ ላይ ተነጥቆ ለሕወሓት ገቢ እንደተደረገም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቷል።

የወያኔው ነፍስ አባት አባ ገብረመድህን ባደረጉላቸው ጥሪ መሠረት ወደ ሃገር ውስጥ የገቡት የግብፅ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሺኖዳ ሳልሳዊ በታሰበላቸው መሠረት ጉብኝት ሳያደርጉ መቅረታቸውን የቤተክህነት ምንጮች ገለጡ።

እንደ ቤተክህነት ምንጮች ከሆነ አቡነ ሺኖዳ ወደ ሃገር ቤት ከመጡ በሁዋላ የተለያዩ ገዳማትንና ታሪካዊ ቦታዎችን እንደሚጐበኙ መርሃ ግብር የተያዘላቸው የነበረ ቢሆንም የፀጥታ ችግር ስለተከሰተ ተሰርዟል ተብለው ፕሮግራሙ እንዳልተካሄደ ገልፀዋል።

በፕሮግራሙ መሠረት ወሎ ላሊበላ፣ ጐንደር ከተማ፣ አክሱም እና ሌሎችም ታሪካዊ ቦታዎችን እንደሚጐበኙ ፕሮግራም የተያዘላቸው ቢሆንም የፀጥታ ችግር የተከሰተ በመሆኑ ተሰርዟል መባሉ በሃገሪቷ ከፍተኛ ችግር እንዳለ አመላካች ነው ሲሉም እነዚሁ የአባ ገብረ መድህን ሰዎች ገልፀዋል፡፡